# የአማራ ዲሞክራቲክ ፓርቲ ልዑካን ስብሰባ በሲያትል

በዘውገ ፋንታ
Seattle 2018

**መግለጫ**

በስልጣን ላይ ያለው ‘የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር’ ተብሎ የሚታወቀው የአራት የፖለቲካ ድርጅቶች ጥምር አካል ነው። ከነዚሁ መካከል ቀንድ የነበረው ‘የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር’ የተባለው አካሉን የፈጠረው አሁን ከሌሎቹ በመለየት አምጾ በሽፍተኝነት መቀሌ ከተማ ተመሽጎ ይገኛል። ከዚያ አካባቢ የሚነፍሰውን አሳፋሪ ወሬ የደሴ አዝማሪዎች በጠላ ቤት መዝናኛ አርገውታል። ከዚያ ባለፈ፣ አሁን የኢትዮጵያን ህልውና የሚከላከሉት ወጣቶች በብዙሃን መገናኛ ተቋማት የጊዜ ማሳለፊያ ዜና አርገውታል። በሌጣ አስተሳሰብ፣ በዚህ ወቅት ደስታን መርጨት ወደር የሌለው የአዕምሮ ህክምና ነው። ከዚህ ለየት ባለ መልክ ደግም ሰፊውን ጊዜ፣ ትልቅ ቁምነገር ባለው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪ ክቡር ጠ/ም ዶ/ር አቢይ የጀመሩትን መሰረታዊ ለውጥ ግንባታ ስራ ከግቡ እንዲደርስ ዜናውን በየደቂቃው ያስተጋባሉ። ኢትዮጵያ የተባረከች ሀገር በመሆኗ የተባረከ ትውልድ በየዘመኑ ይፈጠራሉ። ይህን የሚያረጋግጥ ያለንበት ወቅትና ጊዜ አንዱ ነው።

ቀድሞ ‘የአማራ ሕዝብ ዲሞክራሲያዎ እንቅስቃሴ’ አሁን ‘የአማራ ዲሞክራሳዊ ፓርቲ’ የሚባለው፣ የፌደራሉ መንግሥት አንዱ የክልል አካል ነው። የድርጅቱ የቀድሞ ሊቀመንበር አዲሱ ለገሰ፣ ከሳቸው በኋላ አቶ ደመቀ መኮንን ተተክተው በ ም/ ሊቀመንበር ክቡር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው የፓርቲው አስተዳደር ይካሄዳል። ሌላው የአማራ ድርጂት ነው። መንደሩን፣ ቃየውን፣ ድሀውን፤ የተጎዳውን ሰው የሚረዳ የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው። የአማራ ሰው በብዛት የሚኖርበትን ምድር፣ ጎንደር (በጌምድር)፣ ወሎ፣ ጎጃም፣ ሸዋ፣ መነሻው በማድረግ፣ ሌላውን በቅርሱ የተጣማረውን በኢትዩጵያ ምድር ተሰራጭቶ የሚገኘውን ሰው ሁሉ የጋራ የባህልና የብልጽግና ጥቅሙን ለማራመድ የተደራጀ ነው። ከዚህ በበለጠ፣ የጎሳ ሳይሆን የጎራው ሰው ተሰባስቦና ራሱን አደራጅቶ፣ አገሪቱን ወደ ሰላምና ብልጽግና ጎዳና ለማብቃት ሌት ቀን የሚጥሩትን ጠ/ም አብይን ሙሉ በሙሉ በመደገፍ የተነሳ አካል ነው። ይህ መንፈስ በኢትዮጵያ ምድር ያለው ሰው ሁሉ በየዘርፉ ሆኖ እያስተጋባ ሳለ፣ ባንድ ጎራ ያለው ሰው ያለ ጎሳ መዋቀር ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተጣምሬ ከሌላው አብሬ ለመኖር አልችልም በሚል ሞገድ ተነስቶ፣ መሪውን እንደመሪየ አልቀበልም በሚል አመጽ ወያኔ በመቀሌ ተመሽጎ ይገኛሉ። ማንም ሰው በባዕድ አገር ሆኖ እምቢተኛነቱን ማስተጋባት ይችላሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ በየትኛውም ቦታ በሽፍተኝነት እምብዛም አይሰነብትም።

የተጀመረው ሰፊ የሰላምና የብልጽግና ርምጃ የማይቀለበስ መሆኑን በመሪውና በሕዝቡ ቃል ተረጋግጧል። ከዚህ በኋላ፣ ኢትዮጵያ የግለሰብ መዋቢያና መበልጸግያ እንጂ፣ የደም መፍሰሻና የዕምባ ምድር አትሆንም። ታላቁ ምሑር ፕ/ር መስፍን ስለጊዜው ዕክል ሲናገሩ፣ አንድ ንዑስ ባለጌ አካል የሀገርን ኃይል መፈታተን እንደማይችል ጠቅሰው ይህ ከሆነ መንግሥት እርምጃ ለመውሰድ ግዳጅ እንዳለበት አመልክተዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስልጡን ነው። ሆኖም በአንዳንድ አካባቢ፣ አንዳንድ ሰው አስደንጋጭ የሆነ የስልጣኔ ባህሪ ጉድለት ያሳያል። በሰለጠኑትም ሕዝብ መካከል አለ። አስፈላጊ ሲሆን መቀጣጫ፣ ሲያመች ደግሞ ስለስልጣኔ ኑሮና ባህሪ ሰፊ ትምህርት ያስፈልጋል። ሕብረተሰብ በትጥቅ እራሱን ለመከላከል አስፈላጊ አላስፈላጊም ነው። አስፈላጊ የማያደርገው የመንግሥት ኃይል በየቦታው ጎልቶና ተከብሮ ሲታይና ሲደረግ ነው። ትልቅ ለውጥ በመካሄድ ላይ ስለሆነ፣ ለውጡ በረጋ ሁኔታ ተጀምሮ ያለ ዕክል አያልቅም። ለውጡ መልክ ይዞ ሁሉም እስቲረጋጋ ድረስ፣ ውጣ ውረድ አለ። ጊዜና ትዕግስትን ይጠይቃል። መንግሥት መላ አለው። መላው ለሕዝብ ሳይታወቅ ሲቀር፣ ሕዝብ በጭንቀት ተዋክቦ መንግሥትን ሊያዋክብ ይችላል። መንግሥትም ለዕቅዱ ጊዜ ያጣል። ተዋክቦ እርምጃ ከወሰደ ከግቡ ዘለም ሊል ይችላል። ይህ እንዳይሆን ትግስት ያስፈልጋል። በዚህ ላይ ከማንም ፖለቲካ ሚና ይበልጥ የዜና ተቋማት እጅግ ሰፊና ጥልቅ የሆነ ሂደት ሊፈጽሙ ይችላሉ። የሕዝብን ልቦናና ቀልብ ማብረድ አንዱ ነው። ወያኔ ከቀን ወደቀን የጢስ መውጫ እያጣ ነው። ወያኔ፣ ዘመናዊ በሆነ የሽፍትነት ደባወች ተዘጋጅቷል። ሀገርንና ሕዝብን ለማተራመስ አቅም እንዳለው ገምቷል። የመውደቁ ነገር የቀን ጉዳይ ነው። የክንፈ ዕድልና ጽዋ እንደማይቀርለት በመረዳቱ

አወራጭቶለታል። ኢትዮጵያ የአለምን ስርዐት መጠበቅ አለባት፤ ምሳሌም መሆን ይጠበቅበታል። በምንም ግፊት ተገዳ በምትወስደው ርምጃ የከልብ-ደም የሆነው ቢፈስም፣ ስሟን የሚበክል ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በተቻለ መጠን ግድያን ለመቀነስ ትገደዳለች። ኢትዮጵያ የኢንተርፖል አካል ስለሆነች የአለም ልዑካን ሰተት ብለው አዲስ አበባ ሊመጡና ስራቸውን ሊያካሂዱ ይችላሉ። ሌባና ገዳይን አድነው ይዘው ቆፍድደው ይዘው ቢሄዱ የሚያለቅሰው ያለቅሳል፣ የሚጨፍረው ይጨፍራል።

አዲስ አበባ ትላልቅ የአለም ጉዳዮች የምካሄዱበትና የሚፈጸሙበት መገናኛ ቦታ ናት። የኢትዮጵያን ዕድል ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ተመኝተው ተፎካክረው ነበር። አፄ ኃይለሥላሴና ክቡር ምናሴ ኃይሌ ስማቸው ለዘላለም ተከብሮ ይኑርና፣ የኢትዮጵያ ክብር ከሁሉ በልጦና ጎልቶ እንዲታይ ስላረጉ የታሪክ ቦታዋን ይዛለች። እኒህ እረኞች ይህንን ታሪክ ዘንግተው፣ ኢትዮጵያን እናፈራርሳታለን ብለው ፎከሩ። በቅርቡ ክቡር ጠ/ም አቢይ የመረቁት የገባያ መንደር መልካም ስምና ትልቅ ጸጋን የሚዘረጋ ይሆናል። እግዜር ለወደደው የተባረከ መሪ ሲሰጥ፤ ይህን የነሳው ታይቷል።

**የስብሰባው ውይይት**

በፌደራል ክልል አስተዳደር ስርዓት የተቋቋመው የአማራው አመራር መንግስት (አስተዳደር) በተለያዩ መሪዎች ተመርቷል። ስመ መጥፎው አዲሱ ለገሰ ተነስቶ ክቡር አቶ ደመቀ ሞኮንን ተተክተዋል። ቀድሞ የአማራው ብሔራዊ ዲሞክራቲክ ንቅናቄ ይባል የነበረው የአማራ ዲሞክራታዊ ፓርቲ ተብሎ ተሰይሟል። የዚህ አስተዳደር አመራር ልዑካኖች በም/ ሊቀመንበር በክቡር አቶ ገዱ የሚመራ አካል ወደ ስያትል ከተማ በመምጣት ከኢትዮጵያውያኖች ጋር አስደሳች ውይይት አድርገዋል። ይኽ የውይይቱ አጭር ሪፖርት ነው። በስብሰባው የተገኙት ወገኖች፣ ከቫንኩቨር (ካናዳ)፣ ከፖርትላንድና ከሌሎች አካባቢ ከተሞች የመጡ ነበሩ። ብዙ ሺህ ይገኛሉ ተብሎ ተገምቶ ሳለ፣ ዕለቱ እሑድ በመሆኑ ለተጓዥና ለሌላውም አመች ስላልነበር አንድ ሺህ የማይበልጡ ተገኝተዋል። ስብሰባው በኃይማኖት አባቶች ተባርኮ ተጀመረ። ስለሆነም፣ በተረጋጋ መንፈስ ተካሂዶ ያለ እንከን ተፈጽሟል። የእስልምና ኃይማኖት አባት ኢትዮጵያ በአለም የፍትህ ምድር ተብላ የምትታወቅበትን እርጅም ታርኳን በመተንተን አድማጩን መሰጠው ነበር። የኢትዮጵያዊነትን ኩራት ምንጭ ዘርዝረው ሲያስረዱ ሕዝቡ ደስታውን በሰፊ ጭብጨባ ገልጿል።

ክቡር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው አያሌ ጥያቄዎችን ተቀብለው አስተናግደዋል። አንዳንድ ጥያቄወች የበጎ አድራጎት ድርጅትንና የፖለቲካ ፓርቲን ምግባር አሰበጣጥረዋል። የአማራ ክልል የሚባለው፣ በወያኔ ፌደራል ክልላዊ አወቃቀር መሰረት የሚወክል ነው። የአማራ ድርጂት የሚባለው በሌሎች የሚመራው የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው። አቶ ደጉ ጥያቄዎቹን አመች በሆነ መልክ መልስ እንዲያገኙ አድርገዋል። አንዳንድ ሰው ደግሞ አሁን የሚካሄደው ለውጥ፣ በነበረውና አሁንም ባለው የክልል ድርጅት ቀፎ ስርዐት ውስጥ መሆኑን ባለመረዳት የሚጠይቁትና የሚመኙት ለውጥ አለ። ምናልባት የወያኔ የክልል አሰተዳደርና ህገመንግሥት መቀልበስ እንዳለበት እያመለከቱ ይሆናል። አንዳንድ ለውጦች ለምሳሌ የክልል መታወቅያ ካርዱን ክቡር ጠ/ም አብይ አስፈላጊነቱን ስለፋቁት፣ ሌላውም አስፈላጊ ለውጥ ለምን አልተደረገም የሚል አይነት ብዙ ጥያቄዎች ተሰንዝረዋል። ለምሳሌ ክልሉ፣ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጾችን አስመልክቶ የተነሳ ነው። ይህ መሪው እንደፈቀዱ የሚያደርጉት ሳይሆን የሕዝብ ውሳኔ ነው።

የአማራው የዲሞክራታዊ ፓርቲ የተባለው፣ በጎሳ ማገጥ ውስጥ ያለ ነው። የስም ውበት የሚያሻሽለው ይመስል፣ ሁለት ጊዜ ስሙን ለውጧል። አካሉና ምግባሩ ግን ያው ነው። ይህ ብዙ የሚያስብል ጉዳይ ስላይደለ፣ ይታለፋል። የአማራው ሰው ለኢትዮጵያ ህልውና ሲል ከማናቸውም የበለጠ መስዋዕትነት ከፍሏል። በክልል ጋጥ ውስጥ የሚታሰር አይደለም። በቁጥሩ ተመርዞ ተቀንሷል፣ እጅግ ብዙ ሰው በአካሉ ተኮልሷል። ይህንን ግፍ የተቀበለው የኢትዮጵያን ባንዲራ ከትካሻው አላወርድም በማለቱ ነው። ስሟን፣ ታሪኳንና ቅርሷቿን በማክበሩ ነው። አሁንም ከማንም ባላነሰ ለኢትዮጵያ ልዑላዊነት የቆመ ህዝብ ነው። በምንም ምክንያት ከኢትዮጵያ ሀገራዊ ጉባዔ የሚያስገልለው ኃይል አይኖርም። በውይይቱ የተነሱት ጥያቄዎች፣ በጎሳ የተፈጠረውን የፌደራል አስተዳደር በሚመለከት ላይ ሀሳብ ተሰንዝሯል። ወልቃይት፣ ቅማንት፣ ራያና ቆቦ ሌሎቹም ተጠቅሰዋል።

ሰው ባንድ ቦታ እንደዛፍ የሚተከል አይደለም። እንደውሻም አጥር አይታጠርለትም። የባርነት ስርዓት በነጻ ኢትዮጵያ ላይ ተዘረጋ። ሰው እንደ ንፋስና አእዋፋት የሚዘዋወር ከነዚያም የላቀ ፍጡር ነው። እንስሳ ምድርንና ባህርን አቋርጦ እየተጓዘ የተፈጥሮ ችግርን ይቋቋማል። ድርቀትን እና ክረምትን ያሳልፋል። ሰውም ቢሆን በመሬት ድርቀት ተባሯል። ቅጠሉን አንበጣው ሲጨርሰው፣

የትግራዩ ሰው አካባቢ አገሩን ትቶ በወሎ ሰፍሯል። ወልድያና ደሴ እና ሌሎች ከተሞች የሰፈረባቸው መጠጊያው ነበሩ። ችግሩ አልበረደም፣ ቀጥሎም በሰሜን ወሎ የሚገኘው ባለጸጋ አገርተኛ ወራሪው አንበጣ አወከው። አንበጣው ሰሜን ወሎን አወደመ። የእርሻ ለጋ ቡቃያና ዛፍ ቅጠሉን ግጦ ጨረሰ። የፍጥረት ቢሆንም ተንኮልም ተጨምሮበታል። የኑግሱ አገዛዝ ውድመት በዚያ ሁኔታ ተጀመረ። ሠንሰለቱ ተበጣጠሰ። ማን ይህን ይረዳል? የኢትዮጵያ ሰው ራሱን ሲመቱት እግሩን እያከከ የመጣውን አሳልፏል። በሬውን፣ በጉንና ፍየሉን እያረደ ስደተኛውን ለወራት አበላ። ስደተኛው በየቦታው በተተከለው ድንኳን ምግብ ቀን ሌሊት እየተጓዘ ለወራት ተመገበ። ይህ ጸሐፊ ፎቶግራፍ ለማንሳት ወደ ብዙ ደንኳን ቦታ ሊሄድ ሲሞክር፣ ቤሰቦቹ ከለከሉት። ጉልበት ያገኙት ወደ እርሻ ቦታ ተንዳሆ፣ ጨፋ ሌሎችም ቦታወች ተወስደው ስራ ጀመረ የተደላደለ ኑሮ ጀምረዋል። ከነሱ መካከል አንዱ የነበረውን የትግራይ ልጅ ከዘመናት በኋል ስያትል ይህ ጸሐፊ አገኝቶት ሲያወሩ፣ በወሬ ወሬ ከነዛ ስደተኞች መካከል አንዱ እንደነበረና ተንዳሆ ለብዙ አመት እንደሰራ ነገረው። ያበሉትንና ያጠጡትን ሰወች ደግነት እያስታወሰ አይኑ እንባ ቆጥሮ ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ከትግራይና ወሎ በርሀቡ የተፈናቀለውን አያሌ ሕዝብ በሌሎች ግዛቶች ለማስፈር ዕቅድ ሲያወጣ ምርጥ መሬት ሲፈለግ ካርታው የሰራው ይህ ጸሐፊ ነበር። ትዝ የሚሉት በምስራቅና በምዕራብ ጎጃም ያሉ ቦታወች ነበር። ግን በወባና ሌላ ምክንያት ዕቅዱ ካንዳንድ ቦታ ተቀያይሯል። ይህ ታሪክ ከዚህ የመጠቀሱ ምክንያት ደብረጽዮን ነው።

የዜና ማሰራጫወች ተፈልፍለዋል። የሚያስደስተው ለኢትዮጵያ ልዑልና የእኔ ድምጽ ይበልጣል የሚመስለውን ፋክክር ማየቱ ነው። ተመልካቹና አድማጩ ዳኝነቱን እያጠነከረባቸው ነው። ዜና አስተላላፊዎቹ ነጣም እየተራቀቁ ሄደዋል፣ ዕድሜ ለወያኔ አሻንጉሊቶች። ዜና አቅራቢዎቹ የፓለቲካ ጅል ወይም ሸፋጭ ሴትን ይመርጣሉ። የማይጥምና የማያዋጣ ሰው ቦታ የለውም። ከዚህ በተለየ ለወያኔ ሰው የሚያደርጉት አድልዖ አለ። ሌባም ይሁን ገዳይ የወያኔን ሰው አይጠየፉም። እንደውም ከዕግራቸው ወድቀው ለውይይት እንዲቀርቡ ይለምናሉ። በረከት ሁሉን ብሎ ጨርሷል፣ ግን ከአንገቱ በላይ እየቆረጡ የማናውቀው ሰው እየመሰላቸው አሁንም ያቀርቡታል። በረከት ያላቆሸሸው ቆሻሻ የለም። ኢትዮጵያኖች የሚጠሉትን ስም ሳይቀር በማወደስ ሰድቧቸዋል። ግን፣ ሌሎቹ የሚታሰሩበትን ወንጀል ይጠቁማል። ይህ አስተያየት ከሌላው ቁምነገር እየተቀላቀለ የሚነገረውን ለማመልከት ነው።

የመሪው የዶ/ር አቢይን ንግግር፣ ለብዙኃን ዜና አቅራቢዎች ‘የዕለቱ አስደናቂ ዜና’ ለሚሉት መከፈቻ ነው። ይህ ካልሆነ፣ ‘ያልተነገረ አስደናቂ ወይም አስደንጋጭ ዜና’ ይሉታል። በዚህ የሚቀርበው፣ ‘ነጻነቴ’ እያለ አንዳንድ ያልተለመደ ድርጊት የተፈጸመውን ያቀርባሉ። ወያኔ ቅስታ ሲያሰማ፣ በዚህ ሙያ የላቀው አቶ ጃዋር መሀመድ ይጠራል። ያለጥርጥር ጃዋር በዚያ አርዕስት ላይ ጠለቅ ያለ ዕውቀት አለው። የአፍ ወለምታ የሚያበዛው በሌላው ላይ ሲያነጣጥር ብቻ። ጃዋር ጌታቸው ረዳን ከአይጥ ጋር ያነጻጽረዋል። ወደዚያ መግባት አያስፈልግም። ወደዚያ ሀሳብ የሚያስገባ አንድ ጥያቄ ቀርቦ ነበር። እሱም “የአማራ ክልል ፓርቲ ሲባል እኔ የአዲስ አበባ የሸዋ አማራ ሰው ነኝ። ከጎጃሙ፣ ወሎው፣ ጎንደሩ አማራ ሰው ጋር እታከላለሁ ወይ?”ሲል ጠየቀ። ክቡር አቶ ገዱ ከሰጡት መልስ ተጨማሪ ይህ ጸሐፊ የሚያክለው ሀሳብ አለ። ምናልባት አሁንም ጥያቄውን ያስነሳው የጎሳ አስተዳደር መሰረታዊ ችግር ስላለበት ይሆናል። ለነገሩ ጥያቄው ፕ/ር እስኬል እና አቶ ጃዋር ከሚያራግቡት ሀሳብ ጋር የተያያዘ ነው። እኒህን ታላላቅ ምሑራኖች ማንቋሸሽ ካልሆነብኝ፣ ሀሳቡን እንደቅጡ መግለጽ ያስፈልጋል። እኒህ ሰዎች፣ ቀረብ ለሚሉት ሰው (ጎሳ) ይበልጥ የሚብሰለሰሉ መሆናቸውን ለማሳየት እንጂ የጠቀሱት ታሪክ ክሽፈት መሆኑን ሳያውቁ ቀርተው እንዳልሆነ ይታወቃል። “ፍንፍኔ የማን ናት?” የሚል ታሪክ አንስተው አዋቂውንም ደጉንም አወዛግበዋል። ፍንፍኔ በጣይቱ ዘመን በዱር የተከበበች ትንሽ የግጦሽ ምድር እንጂ ከተማ አልነበረችም። የፍንፍኔ እናት እግራቸውን የኢትዮጵያ አምላክ የተባረከ ስላደረገው፣ የአድዋ አርበኞች መስፈሪያ አረጓት። ከዚያም ቁጥቋጡ እየተመነጠር ጥርጊያ መንገዶች ተዘረጉና በዳር ዳር መደዳ ቤቶች ተሰርተው መናገሻ ከተማ እንዲሆን ተደረገ። ይህንን ከተማ ጣይቱ ዕንቁ ስም በመስጠት አዲስ አበባ አሉት። የንግሥት ጣይቱም ቅድመ - አያቶች ይህንኑ ምድር አልፈው ሰሜን እሻቅበው በመጓዝ የጁ ሰፈሩ። ከዘመናት በኋላ፣ ብሩክ እግራቸውን ወደ እንጦጦ መለሰው! ከዚህ ረግረግ ቦታ ከመሬት ውስጥ እየፈላ የሚፈሰው ፍልውሃ በጦር የናዘለውን አካላቸውን እንዴት እንደፈወሰው ከተረዳን፣ እኒህ አማራ - ኦሮሞ ሴት ምድሩን የባረኩት መሆኑን አምነንት እንቀበላለን። የፕ/ር እስቅየል እና የአቶ ጃዋርን የግልብጥብጦሽ ታሪክ የጣይቱን አጽም የሚያገላብጥ ነው። ለእርግማን ግድ አይኖራቸው ይሆናል። ግን መለስን ሌላውን በቁሙ የሞተውን ማስተዋል ይገባል።

አዲስ አበባና ድሬዳዋ በፌደራል ክልል አመሰራረት መሰረት ራሳቸውን የቻሉ የማንም ጎሳ አካል ያልሆኑ፣ ልዩ የከተማ አስተዳደር መዋቅር ናቸው። የእነዚህ ከተሞች ኗሪ እያንዳንዱ ግለሰብ በዕኩልነት የሚታይ ነው። አስተዳዳሪውን ባለስልጣን የሚመረጠው ኗሪው ሰው ነው። ምናልባት ለመምረጥና ለመመረጥ አንድ ሰው በአዲስ አበባ ነዋሪነቱ ከ (5 ወይም 10) አመት ያላነሰ የሚል ገደብ ቢኖርና ለመምረጥና ለመመረጥ ሲባል የሚከሰቱትን እንከኖች ሊገታ ይችላል። ይኼም በመንግሥት መስሪያ ቤት የሚመደቡ ሰራተኞች በአድልዖና ጉቦ እንዳይጎድፍ ለማድረግ ይጠቅማል። ስለዚህ፣ የአዲስ አበባ አማራ ነኝ፣ ምን ይዋጠኝ ብሎ የጠየቀው ወገን መልሱ፣ የአዲስ አበባ ዜጋ ስለሆንክ፣ ከሁሉ ፍሬ ምጣጭ የተቀላቀልክ፣ የአይንህ ቀለም ከማንም የማይለይህ ኢትዮጵያዊ (አዲስ አበባዊ) ተብለህ ትታወቃለህ። ማንም ኢትዮጵያዊ የሚመኘው እንደዚህ ተጨፍልቶ በእኩልነት መኖርን ነው። ይኽ ሲሆን፣ የአማራ ቅርስህን ልታስተጋባው ትችላለህ። ሌላውም እንደዚሁ። በዚህ መልክ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ባህሎች የሚንጸባረቁባት መስተዋት ናት ማለት ነው። ጥረቱ ሁሉም መንደርና ከተማ እንደ አዲስ አበባ እንዲሆን ነው።

በኢትዮጵያ ያሉ ከተሞች በየጊዜው በሁሉም አቅጣጫ ያድጋሉ። ባጭር ጊዜ በእጥፍ ይሰፋሉ። ይህ የሚሆነው የአካባቢያቸውን ግጦሽ ሜዳ፣ መንደር፣ እርሻና ዱር መሬት እያወገዘ ወደ ከተማ ክልል እየጨመረ ነው። የከተማ አስተዳደር ማንኛውንም መሬት የማውገዝ ስልጣን አለው። ይህ የአለም የከተሞች አስተዳደር መሰረታዊ ደንብ ነው። ያለዚህ ስልጣን የከተማ አስተዳዳሪዎች አይመሰረቱም። ለመንገድ፣ አይሮፕላን ማረፊያ፣ ት/ቤት ማቋቋምያ፣ ሆስፒታል፣ ውሀ ማጠራቀሚያ ሌልም የሕዝብ አገልግሎት ለማቋቀምያ መሬቶች አስፈላጊ ሲሆኑ፣ አስተዳዳሪው መሬቶችን አውግዞ፣ ተመጣጣኝ ካሳ በመስጠት ማንንም ኗሪ የማፈናቀል ስልጣን አለው። የዚህ ጽሕፍ አቅራቢ፣ ፒውጀት ባለሥልጣን ለተባለው መንግሥታዊ አካል በስያትል የባቡር ረጂም ሀዲድ ስር መወገዝ ያለባቸውን ንብረቶች (የመሬትና ህንፃ ዋጋወች) ለባለሥልጣኖች ተምኖ ያቀረበ ስለነበር የሚገልጸው ያለው በሙያ ላይ የተሞረኮዘ ልምድንና ዕውቀትን ነው። አሜሪካ ስለሚኖሩ ይህ ስርዓት ለጃዋርና እስቅየል ግልጽ ነው ተብሎ ቢገመትም፣ ደግም ቢገለጽ ይጠቅማል። ይህን የውገዛ ደንብ የሚያግድ ኃይል ያለው የሕዝብ ወይም የመንግሥታዊ አካል የለም። ይህንን ለማገድ ቅርሳዊ የሆኑ ቤተች ወይም ኃውልቶች ሌላም የኃይማኖት ቦታወች የተለየ አስተያየትን ይጠይቃሉ። ተቀባይነት ባለው የዕድገቱ ዕቅድ እንዲስተካከል በስምምነት ይፈጸማል። የነጃዋርና እስቅየል ጥያቄ፣ ለውጩ አለም አስገራሚ፣ ለኢትዮጵያኖች ማፌዣና መቀለጃ ነው። መንግሥት ዱር መንጥሮ የሰራውን ከተማ፣ አንድ ሰው ወይም ልጆቹ ከመቶ አመት በኋላ 1000 ካሪ ሜትር ለማትበልጥ መሬት ካሳ አይጠይቅም። ይህ ሲባል ፕ/ር እስቅየል ወረዳ ወይም አውራጃ የሆነ አስተዳደር አስበው እንዳልሆነ ይገመታል። የፕ/ር እስቅየል ፍልስፍና አይንና ጆሮ የማያረጋግጠው ነው። ፍልስፍናቸው የራቀና የጠለቀ ቢሆንም፣ የሉሲ ተጓዦች ተንጠብጥበው በየመንገዱ የቀሩትን ዝርክርክ አቅኝወች አሁን ጉራጌ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ወዘተ የሆኑትን ባሰቡ ነበር። እስቅየል፣ ፊንፍኔ አሁን ኦሮሞ የሚባለው ነፍጠኛ ያቀናው ነው ብለዋል። ይህ የማይካድ ታሪክ ነው። ጥንት የጣይቱ አያቶች፣ ኋላም ጣይቱ ተመልሰው እስከ ህይዎት መጨረሻቸው ኑረው ለልጆቻቸው ጥለው ሄደዋል። ይህ ታሪክ፣ ለፕ/ር እስቅየል ያጎት ልጅ ያክስት ልጅ ጠብ ሊሆንባቸው ነው። ለዚህ ታሪክ ማነጻጸሪያ ምሳሌ ለመስጠት ያህል፥ ይህ ጸሐፊ ከሚኖርበት ብዙ የማይርቅ ስፍራ ላይ የ' ችፍ ስያትል' (Chief Seattle) ኃውልት (መቃብር) አለ። ጥያቄውን አስተላለፈ፥ እሳቸውም መለሱ፣ "ያወረሰቻችሁን ጣይቱን ጠይቁ። የእኔ የልጆቼ ጥያቄወች ሌላ ናቸው" አሉ። ይህ የእስቅየልን የረቀቀ ፍልስፍና በተመሳሳይ ለማስረዳት የተደረገ ሙከራ ነው።

የስብሰባው ውይይቱ ቀጥሎ፣ የወልቃይት፣ የአማራው ቅማንት፣ የአማራው ራያና ቆቦ የመሳሰሉት ጉዳዮች ተነሱ። ችግሩ በማግስቱ ተፈጽሟል። በዚች ጽሑፍ ስለነሱ የሚነገር የለም። ቀጥሎ የተነሳው የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች አንድም አማራጭ ሀሳብ አለቀረቡም የሚል ነበር። ዝምታቸው የሚወደድ ሁኗል። የግንቦት ሰባት የአርበኞች ግንባር (የሰላም ኃይሎች?) መሪ ዶ/ር ብርሃኑ የዶ/ር አብይን ሂደት እንደሚደግፉ ገልጸዋል። ስለምርጫው ግን ሙሉ እምነት እንደማይኖራቸው አንጸባርቀዋል። ዶ/ር ክብርት ሚደቅሳ የምርጫው ቦርድ መሪ ስለሆኑ፣ በሳቸው ላይ ሁሉን እምነት መጣል ተገቢ ይሆናል። ኢኃፓ የቆረቆረው ተብሎ የሚነገርለት፣ የመላው ኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ንቅናቂ ተብሎ ሲጠራ የነበረው ወደ ጎሳ ስም ሲቀየር አኩርፎ ወይም ከፍቶት ጎራ ያለ ይመስላል። ምን ይዞ ጉዞ! አቶ ኢያሱ አለማየሁ አዲስ የፖለቲካ ለውጥ ስልትን ይሻል። እንዲሁም የምኤሶን ፓርቲ መሪ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ የጻፉት ድንቅ መጽሐፍ ጠቃሚ ቢሆንም፣ አሁን ጠጋ ብለው ጎልተው መታየት አለባቸው። አረና፣ ሰማያዊ ፓርቲና የኦዲፓ የሚባሉ

የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ። ሰማያዊ ፓርቲ ተከታዮቻቸው በመላ ኢትዮጵያ ላይ ናቸው። በክልል አያምኑም። ሌሎች ሁለቱ በጎሳ ላይ የተመሰረተው ክልላዊ አገዛዝን ይመርጣሉ። ትልቅ ልዩነት ነው። አንቀጽ 39 መደራደሪያ ነው። ዶ/ር ብርሃኑ ስለ ኢኮኖሚ የሕዝቡን ልብ ሊያቀልጡት ይችላሉ። በመሪነት ዶ/ር አብይን ለማስናቅ ከባድ ነው። ጃዋር ውድድር ውስጥ አይገባ፣ ቅጥ ያሳጣዋል። "እነሱ ጡት ቆረጡ፣ እኛ አንገት ቆረጥን!"የሚለው ለዘመናዊ ፖለቲካ አይመችም። ምናልባት ሁለት ምርጫዎች አልፈው ለሶስተኛው ምርጫ ሌላ ትውልድ አርጅቶና በስሎ ያገኘው ይሆናል። ዳውድና ሌንጮ ታዛዥ ተከታይ የላቸውም። ወደ ቀኝ ሲሉት ወደ ግራ የሚጎርፍ ሰው ነው። ምነው በቀኝ ሲሉት ወደ ግራ ሄዱባችሁ? ሲሏቸው፣ አዎ፣ ሰው ቀድሞ ወደቀኝ ብለነው ወደ ግራ ከሄደ፣ በዚያው ቦታ ተገኝተን እንመራዋለን፣ ችግር የለም የሚሉ ሆነዋል።

***መደምደሚያ***

የፖለቲካ ተቋማት ለብዙ ጊዜ የኢትዮጵያን ጥቅም እያበሰሩ ገዝግዘው ወያኔን ገርምስሰዋል። ከላይ የጠቀስኳቸው ሁሉ ወደር የሌለው መስዋዕትነት ከፍለዋል። ለወደፊትም የበለጠ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ኢትዮጵያ ለነሱ ሰፊ ክብርና ቦታ መስጠት ይኖርባታል። ዕንቁው ነገር የጠ/ም አቢይን ለውጥ አጥብቀው ይደግፋሉ። ይህ ወደር የማይገኝለት የፖለቲካ ብስለት ነው። መንግሥት ቅንጣት ዕውቀት ያለጥቅም እንዳትጠፋ ለማድረግ ያመቻል። ሌላው ቁምነገር ጠ/ም አቢይ ኢትዮጵያ ልጆቿን እንድትሰበስብ እጇን መዘርጋቷና በሩን መክፈቷ ነው። ፕ/ ኢሳኢያስ አፈውርቂ ለጋራ ብልጽግና ምንም እንከን በማይገኝለት መንገድ እንደሚተባበር የማንም ህሊና የሚረዳው ነው። ስለዚህ ወርቅ ዘመን ወደፊት አለ። ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ በጥያቄ መልክ የግልና የቤተሰብ ችግሮች ጎልተው በአሳዛኝ መልክ ተነግረዋል። የአማራው መንግሥት የሚያከናውነው ሰፊ ስራ አለ። የአማራው የበጎ አድራጎት ድርጅትም እንዲሁ ሰፊ ስራ ይጠብቀዋል። እንደነ ብ/ጀ አሳምነው ጽጌ ያሉበት አካል ስለሆነ አሁን የሚያሳስበው ጉዳይ ከትንሽ ጊዜ በኋላ መልኩ ይለወጣል። በልዕካኖቹ ላይ ያነጻጸረ ጥያቄ ተነስቷል። መፍትሄ በሚያመጣ አካል ላይ ለውይይት ቢቀርብ መልካም ነው። ልዕካኖቹ አያሌ የስራ ዕቅድ አቅርበዋል። እጅግ የሚደነቅ ዕቅድ ነው።

ስብሰባው በጥሩ ተካሂዷል። አዘጋጆቹ መሞገስ አለባቸው። አንዱን አንስቶ ሌላውን መተው አጸያፊ ነው። ግን አንዱን የመድረክ አስተናጋጅ የነበረውን ለይቶ መጥቀስ አያስቀይምም። በዕውነቱ ምክትሉም ሁሉም ቢጠቀሱ ጥሩ ነበር። ደስ የሚያሰኝ ስራ ሰርተዋል። ስያትል በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተቀዳሚ ሆና ኖራለች። ለወደፊትም በብልጽግና ሂደቶች ላይ እንዲሁ በስያትል የሚገኘው የኢትዮጵያ ወገን ትልቅ አስተዋጽዖ ለማድረግ ኃይል ነው።

**አለቀ**

በዚህ ሪፖርት ላይ ጥያቄ ካላችሁ

Please contact:

zegfantam@aol.com or

zegfanta57@gmail.com